# ለክርስቶስ መኖራችን በመንፈሳዊ እድገት ይገለጥ!

## ቆላስይስ 1፡9-14

## መግቢያ

የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው ጳውሎስ በኤፌሶን ለሦሥት ዓመት ባገለገለበት ጊዜ ኤጳፍራ የተባለው ሰው የጌታን ቃል ሰምቶ ከተለወጠ በኃላ ወደ ቆላስይስ በመሄድ ወንጌልን በማድረሱ ምክንያት ነው (ቆላ 1፡7፤ሐዋ 19፡10)፡፡ የቆላስይስ መልዕክት የተጻፈው ጳውሎስ በሮም ራሱ በተከራየው ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመት ያህል በእስር ላይ በነበረበት በመጀመርያ እስራቱ ወቅት እንደሆነ ይገመታል (ሐዋ 28፡16-31)፡፡ የተጻፈውም በ 60 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ መልዕክት የተጻፈው ስለ ስህተት ትምህርት የተነሱ ጥያቄዎችን መልስ ለመስጠት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚያ በፊት ጳውሎስ ከኤጳፍራ በሰማው መሰረት (1፡8) የቆላስይስን ክርስቲያኖች ስላላቸው ***እምነት***፣ ***ተስፋና ፍቅር*** በማመስገን ስለ ሁለት ነገሮች ደግሞ ጸልዮላቸዋል፡፡ የጳውሎስ ጸሎት <u>በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡</u>

ታዲያ እነዚህ ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች የጸለየላቸው ሁለት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? አሁን በዚህ ዘመን ላለነው ክርስቲያኖችስ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው? እነዚህን ሃሳቦች እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

1. **<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ (1፡9)</u>፡፡**

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የመንፈሳዊ እድገት ዋነኛ መሰረት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ትኩረቱ/የሚያነጣጥረው በክርስቶስ ላይ ነው፡፡

<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለማወቅ ልንረዳቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮች አሉ፡፡</u>

ሀ) <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ከእግዚአብሔር ቃል መረጃን (information) በማግኘት ይጀምራል፡፡</u>
- የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው፡፡
- የመንፈሳዊ እድገት መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡

ለ) <u>ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ስለ እግዚአብሔር መረጃን (information) በአእምሮአችን ከማከማቸት ያልፋል፡፡</u>
- ይህ እውቀት ለሕይወት በሚጠቅም መንገድ ከሕይወታችን ጋር መዋሃድ/መዛመድ አለበት፡፡
- ለዚህ ነው ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ ጋር ***<u>መንፈሳዊ ጥበብ (wisdom)</u>*** እና ***<u>መንፈሳዊ መረዳት (አእምሮ) (understanding)</u>*** ይሞላባቸው ዘንድ እግዚአብሔርን የለመነው፡፡ (1፡9)
- መንፈሳዊ ጥበብና መረዳት እውቀት ወደ ተግባር እንዲለወጥ ያደርጋል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅና ጥቅስ ብቻውን መጥቀስ መንፈሳዊ እድገትን አያመጣም፡፡ ለዚህ ነው፡- <u>"እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርህሩሆች ሁኑ፤"</u> (ኤፌ 4፡32) እያልን ጥቅስ እየጠቀስን ነገር ግን እርስ በርሳችን በቃል የምንገዳደለውና አንዳችን በሌላችን ላይ ጨካኞች የምንሆነው፡፡

ሐ) <u>እውነተኛ የሆነ እውቀት ሁልጊዜ የባህሪይ ለውጥ ያስከትላል፡፡</u>

- የባህሪይ ለውጥ የማያመጣ እውቀት ምንም ትርፍ የለውም፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ፡- ***<u>"ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን፣"</u>*** (2 ጢሞ 3፡7) በማለት የተናገረው፡፡ በሌላ በኩል የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ፡- ***<u>"የእውነት እውቀት ከተቀበልን በኃላ ሆን ብለን በሃጢአት ጸንተን ብንመላለስ ከእንግዲህ ለሃጢአት የሚሆን ሌላ መስዋዕት አይኖርም፡፡"</u>*** (ዕብ 10፡26 - አ.መ.ት.) በማለት ተናግሯል፡፡
- ይህ የሚያሳየን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቃችን የግድ የባህሪይ (የሕይወት) ለውጥ ማምጣት እንዳለበት ለማሳሰብ ነው፡፡
- ለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- ***<u>"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡"</u>*** (ማቴ 7፡21) በማለት ጠንካራ ቃል የተናገረው፡፡

2. **<u>ለክርስቶስ እንደሚገባ በመኖር ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በማደግ በሁሉም እርሱን ደስ እንዲያሰኙ፡፡ (1፡10-14)</u>**

ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች የጸለየላቸው ሁለተኛው ጸሎት ለክርስቶስ እንደሚገባ በመኖር ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በማደግ እርሱን ደስ እያሰኙ እንዲኖሩ ነው፡፡ መንፈሳዊ እድገት ለጌታ እንደሚገባ የምንኖርበትና በሁሉም አቅጣጫ እርሱን ደስ የምናሰኝበት መንገድ ነው (1፡10*ሀ*)፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ በተጨባጭ የሚገለጥ ነው፡፡ አንድ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደጉ ወይም ሕይወቱ ለመለወጡ ግልጽ የሆኑ ምልክቶች ወይም ማረጋገጫዎች አሉ፡፡ መንፈሳዊ እድገት መለኪያ የሌለው ሳይሆን ግልጽና ተጨባጭ የሆኑ ማስረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ማረጋገጫዎች በአማኙ ሕይወት የሚገለጡ ናቸው፡፡ ለዚህ እንዲረዳን የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ምልክቶችን ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡

**<u>የመንፈሳዊ እድገት (የሕይወት ለውጥ) ተጨባጭ ምልክቶች፡፡ (1፡10-14)</u>**

*ሀ*) <u>በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ አማኝ በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ ያፈራል፡፡</u> (1፡10ለ)
እነዚህ ፍሬዎች ደግሞ በገላትያ 5፡22-23 ተጠቅሰዋል፡- ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ እና ራስን መግዛት ናቸው፡፡
እነዚህ ደግሞ አንድ አማኝ የክርስቶስን ሕይወትና ባህሪይ በራሱ ሕይወት ለሌሎች በተጨባጭ የሚገልጽበት ብቸኛ መንገዶች ናቸው፡፡

ለ) <u>በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ አማኝ እግዚአብሔርን በማወቅ ያድጋል፡፡</u>(1፡10ሐ)
እግዚአብሔርን በማወቅ የምናድገው ዕውቀትን በማከማቸት ብቻ ሳይሆን ያወቅነውን ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ በተግባር እየኖርን ስንለማመደውና እግዚአብሔር በግላችን በሚገባ ስናውቀው ነው፡፡ ምግብ ወስደን በሚገባ ተፈጭቶ በሰውነታችን እንደሚገባ ካልተሰራጨ በስተቀር ለሰውነታችን ምንም ጥቅም አይሰጥም፡፡ ይልቁንም የወሰድነው ምግብ ጤንነታችንን ያውካል፡፡ በተጨማሪ የምግብ ፍላጎታችንን (appetite) ይዘጋናል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔር ቃል ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በተግባር በሕይወታችን ካልኖርን ወይም የምናውቀው ቃል ሕይወታችንን በመለወጥ ጤነኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድንኖር ካላደረገን የእውቀት ሰዎች ብቻ በመሆን በተግባር ግን የክርስቶስ ሕይወት የማይገለጥብን እንሆናለን፡፡ በተጨማሪ እውቀትን በማከማቸታችን ምክንያት

ብቻ አዋቂዎች እንደሆንን ስለምናስብ የእግዚአብሔር ቃል ፍላጎታችን (appetite) ይዘጋል፡፡ ለመማር ፈቃደኞች አንሆንም፣ ፍላጎቱም አይኖረንም፡፡
የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቁ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር በመወሰን ራሳቸውን ለፈቃዱ ሲሰጡ ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ ሳይሆን ራሱን እግዚአብሔርን ያውቁታል፡፡

ሐ) <u>በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ አማኝ በሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ታላቅ ፅናትና ትዕግስት ይኖረዋል ፡፡</u>(1፡11ሀ)
በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደጉ አማኞች በሁኔታዎች ሁሉ የሚናወጡና ወዲህና ወዲያ የሚንገዳገዱ አይሆኑም፡፡ ተንሳፋፊዎች አይደሉም፡፡ በፅናትና በትዕግስት የተሞሉ ናቸው፡፡
***“ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኃላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኮልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕጻናት አንሆንም፡፡ ይልቁንም እውነትን በፍቅር እተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው፡፡”*** (ኤፌ 4፡14-15 - አ.መ.ት.)
***“ምንም የማይጎድላችሁ ፍጹማንና ምሉአን እንድትሆኑ ትዕግስት ሥራውን ይፈጽም፡፡”*** (ያዕ 1፡4 - አ.መ.ት.)

መ) <u>በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ አማኝ እንደ እግዚአብሔር ጉልበት መጠን በሃይል ይበረታል/የተሃድሶ ሕይወት ይኖራል፡፡</u> (1፡11ለ)
***“ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፤ ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፣ አይደክሙም፡፡”*** (ኢሳ 40፡30-31)

ሠ) <u>በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ አማኝ ደህንነቱን እያሰበ በሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር አብን እያመሰገነ በደስታ ይሞላል፡፡</u> (1፡11ሐ-14)
በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደጉ ሰዎች ስለተቀበሉት ደህንነት በሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑና ደስ በመሰኘት የሚኖሩ ናቸው፡፡

***<u>ማጠቃለያ</u>***
እግዚአብሔር ለእኛ ያለው የመጨረሻ ዓላማ መንፈሳዊ እድገት ነው፡፡ መንፈሳዊ እድገት ደግሞ ክርስቶስን መምሰል ነው፡፡ ወደ ክርስቶስ ሙላት መድረስ ነው፡፡ ለዚህ ነው ኢየሱስ ፡- ***“እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡”*** (ዮሐ 10፡10) እንደዚሁም ***“ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኃችሁ፡፡”*** (ዮሐ 15፡6) በማለት እርሱን በማመን ለተከተሉት ለደቀመዛሙርቱ በአጽንዖት የተናገረው፡፡
የእውነተኛ አገልጋዮችም የአገልግሎታቸው ዋነኛ ዓላማ የአማኞች መንፈሳዊ እድገት ነው፡፡ ጳውሎስ ***“እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሰጽን ሰውንም በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው፤”*** (ቆላ 1፡28) በማለት የአገልግሎት ዓላማውን ግልፅ አድርጓል፡፡
ስለዚህ እኛም ጥሪያችንን በመረዳት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ፣ እንደ ፈቃዱ በመመላለስና ለክርስቶስ የሚገባ ሕይወትን በመኖር ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን በማደግ ክርስቶስን ደስ እያሰኘን ልንኖር ይገባናል፡፡

***ለክርስቶስ መኖራችን በመንፈሳዊ ሕይወታችን በማደግ ይገለጥ!***